# ቄሳርና አብዮት

አብርሃም በየነ

ያንድ ወንዝ ቅጅዎች የፊውዳል መልከኛ

አንዱ የገዥ መደብ አንዱ አብዮተኛ

ታጋዩ ለመስበር የጭቆናን ቀንበር

ገዥውም ላለመውረድ ከስልጣኑ ወንበር

ግብ ግቡ ጡዞ ፍትጊያው ሲጀመር

በሞት ምጣድ ገብቶ ይታመሳል አገር።

ጭቆናን ለማጥፋት የመጣው አብዮት

አገር አተራምሶ የለውጡ ስርየት

ስንት ቤት አፍርሶ

ስንት ደም አፍስሶ

አብዮቱ ቄሳር ይሆናል መልሶ።

ጥቅምት 2003